የሰበር መ/ቁ 50838

ሚያዝያ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት - ነገረ ፈጅ አንድአርጋቸው በየነ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ አማረ አበራ

2. አቶ ሽፈራው ጉደታ

3. አቶ ጌታቸው ይማም

4. አቶ አስማረ ቢሆነኝ

5. አቶ መሐመድ ሰይድ

6. አቶ እሸቱ ማሞ

7. አቶ አያሌው አሠፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ታህሳስ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪዎች በከሳሽነት በመቅረብ ተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር በነበረበት ወቅት ለሀያሁለት ዓመት በፎርማንነት የሥራ መደብ አገልግለናል፡፡ የተንዳሆ እርሻ ልማት ፈርሶ ወደ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በመንግስት ውሣኔ ሲዛወር የሠራተኞች መብት ጥቅም መጠበቅ እንዳለበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 131/99 ተደንግጓል፡፡ ከሳሽ (አመልካች) መዋቅር ሲያፀድቅ የእኛን የሥራ መደብ መያዝና ማፅደቅ ሲገባው አፍርሶታል፡፡ ስለዚህ ከሙያችንና ከልምዳችን ውጭ በሆነ ሁኔታ ደረጃችንን ዝቅ አድርጎ የመደበን በመሆኑ ተንዳሆ እርሻ ልማት ስንሠራ በነበርንበት የፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድበን በማለት አመልክተዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ እየተደራጀ ያለው ከተንዳሆ እርሻ ልማት የተለየ አዲስ ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለው አዲስ መዋቅር ዘርግቷል፡፡ ጥቅማቸውን በማይቀንስ ሁኔታ ባለው መዋቅር መድበናቸዋል፡፡ ድርጅቱ በሌለው የፎርማንነት የሥራ መደብ ለመመደብ ያቀረቡትን ጥያቄ የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ አመልካች ተጠሪዎችን በፎርማንነት የሥራ መደብ ይመድባቸው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ክርክሩ ግላዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ በመነሳት አደረጃጀቱና መዋቅሩ ተቀይሯል፡፡ ስለዚህ በሌለ የሥራ መደብ ተጠሪዎችን እንድንመደብ የሰጠው ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ የሚቃረን በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መሠረታዊ ቅሬታችን የሀያ ሁለት

ዓመት አገልግሎታችንን ወደ ጎን በመተው የሠራተኛ ማህበር ተወካይ ባልተገኘበት በአዲስ የሥራ መደብ ላይ በመመደባቸው ነው፡፡ ሥለዚህ ቦርዱና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በስር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች አዲስ በዘረጋው መዋቅር የሥራ መደባችን ፈርሷል፡፡ ስለዚህ በፊት የነበረንን የሥራ መደብ በአዲሱ መዋቅር በማካተት በፊት በሠራንበት የሥራ መደብ በፎርማንነት ይመድበን በማለት ነው፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄና የሚሰጠው ውሳኔ በእነርሱ ብቻ የሚወሰን ውጤት ያለው ሣይሆን የሌሎችንም ሠራተኞች ለተመሣሣይ ጥያቄ የሚጋብዝ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው ነው፡፡ ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ባህሪ ያለው በመሆኑ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ የአመልካችንና የተጠሪዎችን ክርክር ሰምቶ የመወሰን ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 147 መሠረት አለው፡፡ ስለዚህ አመልካች ቦርዱ ጉዳዩን መርምሮ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ቦርዱ ጉዳዩን የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረስን በኋላ የቦርዱ ውሣኔ ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክት በፊት ከነበረው የተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር የተለየ የሥራ ባህሪ ያለው ድርጅት ነው፡፡ አመልካች ለሥራ ባህሪው የሚስማማ የሥራ መዋቅርና የሥራ መደብ በጥናት ላይ በመመርኮዝ እንዲፀድቅ በማድረግ የሠራተኛ ምደባ አከናውኗል፡፡ ተጠሪዎች በፊት ያላቸው የሥራ ልምድና የትምህርት ዝግጅት አዲስ ለፀደቀው የሥራ መዋቅር የትኛው ቦታ ላይ ሊያስመድባቸው እንደሚችል በኮሚቴ ተጠንቶና ታይቶ በፊት ያገኙት የነበረው ደመወዝ ሣይቀነስ በአዲሱ የሥራ መዋቅር አዲስ ሥራ መደብ ላይ ተመድበዋል፡፡ ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራውን ለማከናወንና አትራፊና ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችለው አደረጃጀትና የመደራጀትና የሥራ መደብ የማዋቀር ሥልጣን እንዳለው ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች የተጠሪዎችን ደመወዝ ሣይቀንስ በአዲሱ መዋቅር ሊመጥናቸው በሚችለው የሥራ መደብ መድቦ የማሠራት ሙሉ ኃላፊነት ያለው ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በአዲሱ መዋቅር ባልተካተተና በሌላ የሥራ መደብ አመልካች ተጠሪዎችን መድቦ እንዲያሠራ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ሠራተኞችን ባለው መዋቅርና አደረጃጀት መድቦ የማሠራት መብት የሚጋፋውን የቦርዱን ውሣኔ በይግባኝ ሣያርም ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ